በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 211654
ቀን ፡- የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- መዓዛ አፈወርቅ የእንጨት መሰንጠቂያ፣ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ድርጅት፡- ጠበቃ ጋሻዬ አወቀ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ስማቸው ባዩህ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በግል የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሥራ ውል መቋረጡ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ ስሰራ የ2010 ቅጥረኛ ፎርም እንድሞላ በመጠየቅ ለዚህም ፈቃደኛ ባለመሆኔና መብቴን በመጠየቄ አመልካች የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ ስላቋረጠ ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ እንዲከፍላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ያቀረበው መልስ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው የድርጅቱ ሥራ በመቀዛቀዙና ሁኔታው ለተጠሪ ተገልጾና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎ የተፈጸመ የሥራ ውል ማቋረጥ ተግባር ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 90858 የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ መቀዛቀዙን አስረድተዋል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች የተሰናበቱት ውል ፈርሙ በመባላቸው መነሻነት ስለመሆኑ ያስረዱ ቢሆንም ምስክሮች በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ የነበሩና የለቀቁ ከመሆናው አንጻር እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት የሠራተኛ ቅነሳ ተግባር መፈጸሙ ሕጋዊ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝ የተቀበለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ እና ማስረጃውን በድጋሜ መዝኖ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ደመወዝ ቀንሰው የሥራ ውል ፈርሙ በመባላቸውና ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መሆኑን አስረድተዋል፤ ምስክሮቹ ቀደም ሲል የአመልካች ድርጀት ተቀጣሪ ሠራተኛ መሆናቸው እምነት እንዳይጣልባቸው የሚያደርግ አይደለም፡፡ አመልካች ይህን ማስረጃ አላስተባበለም፡፡ የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ ስለመቀዛቀዙ ያስረዱ ሲሆን ስራው በመቀዛቀዙ የተሰናበቱ ሠራተኞች ስም ዝርዝርም በሠነድ ማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ነገር ግን የቀረበው ማስረጃ የድርጅቱን ሠራተኛ አቅርቦ ሥራው ቀዝቅዟል ከማለት ባለፈ ሥራው በትክክል ስለመቀዝቀዙና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት ተጠሪን ከሥራ ሊያስቀንስ የሚችል ሁኔታ መከሰቱን በአግባቡ አላስረዳም፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው፤ ተጠሪ የሥራ ውላቸው ሲቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የተከፈላቸውና ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው በመሆኑ ያልተከፈላቸው የስድስት ወር ደመወዝ በካሣ መልክ ብር 26,520.00 አመልካች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም ነበር፡፡ የድርጅቱ ተፈላጊነትን መቀነስን አስረድተን በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ እያለ ሕገ-ወጥ ስንብት መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የሥራ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28 አንጻር አግባብነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ባቀረቡት መልስ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታው ምክንያቱና ማስረጃው ተመዝኖ በአግባቡ የተወሰነ ነው፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ ምዘናን አይመለከትም፡፡ ከሥራ የተሰናበትኩት የደመወዝ መጠኑ ተቀንሶ ውል እንድፈርም በማዘዙና ባለመቀበሌ ስለመሆኑ በሚገባ አስረድቻለሁ፤ አመልካች የድርጅቱ ሥራ ስለመቀዛቀዙ አለማስረዳቱ ተረጋግጦ የተወሰነ ውሳኔ ስለሆነ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የተጠሪዎች የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመጀመሪያ አመልካች ከይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ጋር አያይዞ ያቀረበውን ክርክር እንደተመለከትነው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ራሱ ችሎ አቤቱታ ቀርቦበት ከይግባኙ መዝገብ በተለየ ፋይል ቀርቦ የሚወሰንና በውሳኔውም ላይ እንደሁኔታው የይግባኝ ሆነ የሠበር አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ይግባኝ ማስፈቀጃ አቅርበው የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ ከግራቀኙ ክርክር የተገነዘብን ቢሆንም ውሳኔው ከዚህ የሰበር አቤቱታ ጋር ተያይዞ ያልቀረበና የሠበር አቤቱታው መነሻ ያደረገው የሥረ-ነገሩ ክርክር ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመሆኑ አመልካች ከይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

የጉዳዩን ሥረ-ነገር እንደመረመርነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ ስሰራ የ2010 ቅጥረኛ ፎርም እንድሞላ በመጠየቅ ለዚህም ፈቃደኛ ባለመሆኔና መብቴን በመጠየቄ አመልካች የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ አቋርጧል የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው የድርጅቱ ሥራ በመቀዛቀዙና ሁኔታው ለተጠሪ ተገልጾና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎ የተፈጸመ የሥራ ውል ማቋረጥ ተግባር ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ መቀዛቀዙን አስረድተዋል፤ የተጠሪ ምስክሮች የተሰናበቱት ውል ፈርሙ በመባላቸው

መነሻነት ስለመሆኑ ያስረዱ ቢሆንም ምስክሮች በአመልካች ድርጀት ሲሰሩ የነበሩና የለቀቁ ከመሆናው አንጻር እምነት የሚጣልበት አይደለም፤ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት የሠራተኛ ቅነሳ ተግባር መፈጸሙ ሕጋዊ ነው በማለት ክሱን ውደቅ ያደረገ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በበኩሉ ማስረጃውን በድጋሜ መዝኖ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ደመወዝ ቀንሰው የሥራ ውል ፈርሙ በመባላቸውና ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መሆኑን አስረድተዋል፤ ምስክሮቹ ቀደም ሲል የአመልካች ድርጀት ተቀጣሪ ሠራተኛ መሆናቸው እምነት እንዳይጣልባቸው የሚያደርግ አይደለም፡፡ አመልካች ይህን ማስረጃ አላስተባበለም፤ የአመልካች ምስክሮች የድርጅቱ ሥራ ስለመቀዛቀዙ ያስረዱ ሲሆን ስራው በመቀዛቀዙ የተሰናበቱ ሠራተኞች ስም ዝርዝርም በሠነድ ማስረጃነት ቀርቧል፤ ነገር ግን የቀረበው ማስረጃ የድርጅቱን ሠራተኛ አቅርቦ ሥራው ቀዝቅዟል ከማለት ባለፈ ሥራው በትክክል ስለመቀዝቀዙና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት ተጠሪን ከሥራ ሊያስቀንስ የሚችል ሁኔታ መከሰቱን በአግባቡ አላስረዳም፤ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመለየት፣ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን በተሰጠው ኃላፊነት ተጠሪ የተሰናበቱት ደመወዝ ቀንሰው የሥራ ውል ፈርሙ በመባላቸውና ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ስለመሆኑ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የማስረጃ ምዘና ሂደት የተፈጸመ የማስረጃ ሕግና ማስረጃ ምዘና መርሕ ጥሰት መኖሩን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የሥራ ውል ከሕግ ውጭ ስለተቋረጠ ካሣ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 267829 ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ